የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
# ADDIS NEGARI GAZETA
OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፸፭
አዲስ አበባ ታህሳስ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Eighth year No.75
Addis Ababa December 18, 2015

**ማውጫ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣም ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ……………………………………………ገፅ ፩

**CONTENTS**

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT RIVERS AND RIVER SIDES DEVELOPMENT AND CLIMATE CHANGE ADAPTATION PROJECT OFFICE REGULATION…………………...... PAGE 1

## ደንብ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፰

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣም ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ወንዞች፣ ገባሮች እና የወንዝ ዳርቻዎች ከተለያዩ የመኖሪያ ቤቶች፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም የከተማዋን የወንዝ ዳርቻዎችን ተከትሎ ከተመሰረቱ ፋብሪካዎች በሚወጣው አደገኛ በካይ ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻዎች ምክንያት ነዋሪዎች ለተለያዩ የጤና ችግሮች የተዳረጉ ከመሆናቸውም በላይ ከተማዋ በአካባቢያዊ እና ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለዉጥ ተጽዕኖ ተጋላጭ እየሆነችና ሥጋትም እየተጋረጠባት በመሆኑ፣

## REGULATION No.75/2015

## A REGULATION TO PROVIDE FOR ESTABLISHMENT OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT RIVERS AND RIVER SIDES DEVELOPMENT AND CLIMATE CHANGE ADAPTATION PROJECT OFFICE

**Whereas**, the health condition of the dwellers of Addis Ababa City has been suffering from the pollution resulting from dangerously polluted liquid and solid wastes of rivers, their tributaries and river banks found in Addis Ababa generated from different residential areas, service rendering institutions and industries established across the rivers and the City has become exposed to regional and international climate change and such has become potential threat;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ወንዞች እና የወንዝ ዳርቻዎች ከግምባታ፣ ከብክለት በመከላከል ወንዞች ተፈጥሯዊ ባህሪያቸውን እንዲይዙ እና ከአየር ብክለት ለውጥ ጉዳት ለመታደግ፣ በህዝብና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ንፁህ ማራኪ እና አረንጓዴ በማድረግ፣ ነዋሪዎችና ጎብኝዎች የሚዝናኑበት አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የወንዝ ዳርቻ መገንባት እና በከተማዋ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን የአየር ንብረት ለዉጥን መከላከልና በተከሰተም ጊዜ በማጣጣም ለአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር ከተማ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀፅ ፳፫(፩)(ረ) እና የአስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ አንቀጽ ፹፬ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርእሰ**

ይህ ደንብ "የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣም ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ደንብ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "**አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

**Whereas**, it has become necessary to protect Addis Ababa City Rivers and River Sides from construction, and pollution to keep their natural features; to safeguard from air pollution, to make them clean, catchy, and green through the participation of the public and the stakeholders; to build an international recreational standard river banks that would enable recreational center for the dwellers and tourists and to prevent climate change on the City as well to create a City resistant to such by adapting in case it occurs;

**Now, therefore**, in accordance with Article 23/1/(f) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No.361/2003 and Article 84 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No.35/2012 the City Government Cabinet issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as "The Addis Ababa City Government Rivers and River Sides Development and Climate Change Adaptation Project Office Regulation No.75/20015".

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1. "**Government**" means the Addis Ababa City Government;

፪. "**ሥራ አስኪያጅ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ ነው፤

፫. "**ቦርድ**" ማለት ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ አባላት ያሉበትና በከተማዉ ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በከንቲባው የሚሰየም የፕሮጀክት ጽኅፈት ቤቱን በበላይነት የሚያስተዳድር ነው፤

፬. "**ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት**" ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ነው፤

፭. "**ብክለት**" ማለት በዚህ ደንብ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገ ማንኛውንም ግዴታ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውንም አካባቢ ክፍል ቁሣዊ፣ ጨረራዊ ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረ ነገራዊ፣ ስነሕይወታዊ ወይም ሌላ ባህሪ በመለወጥ የተፈጠረ፣ በሰው ጤና ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያውያን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤

፮. "**የአካባቢ ብክለት**" ማለት በአካባቢ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ላይ ለውጥ በማስከተል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሕይወት፣ በግንባታዎች ወይም በሰው ልጅ ተለምዷዊ ኑሮ ላይ ጉዳት ማድረስ ነው፤

፯. "**አደገኛ ነገር**" ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ጋዝ፣ ተክል፣ እንሰሳ ወይም ረቂቅ ህዋስ ነው፤

2. ''**Manager**'' means the Addis Ababa City Government General Manager;

3. ''**Board**'' means the higher administrative organ of the project office, the members of which are appointed by the Mayor upon recommendation of the Manager;

4. ''**Project Office**'' means the Addis Ababa City Government Rivers and River Side's Development and Climate Change Adaptation Project Office established pursuant to this Regulation;

5. ''**Pollution**'' means any condition which is hazardous or potentially hazardous to human health, safety, or welfare or to living things created by altering any physical, radioactive, thermal, chemical, biological or other property of any part of the environment in contravention of any condition, limitation or restriction made under this Regulation and any other relevant laws;

6. ''**Environmental pollution**'' means any change in the natural environment that directly or indirectly affects the life, construction or day to day activities of human being;

7. ''**Hazardous material**'' means any substance in solid, liquid, gaseous state or any plant, animal or micro organism that is injurious to human health or the environment;

፰. "**አደገኛ ቆሻሻ**" ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው፤

፱. "**መልቀቅ**" ማለት ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ነገር ወደ አካባቢ መጨመር ነው፤

፲. "**የወንዝ ዳርቻ**" ማለት በከተማው መሪ ፕላን ወይም በዝርዝር ጥናትቶች መሰረት ለወንዝ ዳርቻ መጠበቂያ ተብሎ የተከለለና ለሌላ ለማንኛውም ዓይነት ግንባታ አገልግሎት እንዲውል የማይፈቀድ ቦታ እና በወንዙ ቀጥተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም የሚያድርበት ሥፍራ ነው፤

፲፩. "**ወንዝ**" ማለት በከተማው መሪ ፕላን መሰረት ከአንድ የተወሰነ ቦታ የሚመነጭና በትናንሽ ገባር ፈሳሾች ዳብሮ ረጅም ርቀት የሚጓዝ ወራጅ ውሃ ነው፤

፲፪. "**ጥበቃ**" ማለት የተፈጥሮ ባህሪይ እንዳይናጋ በመጠበቅና የተፈጥሮ ሃብቶች ምንጭ አቅምን በማጎልበት የአሁኑ ትውልድ ፍላጎት የማርካት ሂደት የመጪውን ትውልድ ሳይጎዳ እንዲያሟላ ማስቻል ነው፤

፲፫. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎችና በከተማዉ የአየር ንብረት ክልል ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**፬. <u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹት ለሴት ፆታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

8. ''**Hazardous waste**'' means any unwanted material that is believed to be deleterious to human safety or health or the environment;

9. ''**Emission**'' means disposing of any pollutant in the environment in any way be it intentionally or otherwise;

10. ''**River sides**'' means a place demarcated as a preserved river bank area in accordance with the master plan of the City and not permitted to be used for any construction services as well as which has influence on or influenced by the river;

11. ''**River**'' means flowing water streamed from specific area according to the master plan of the City and strengthened with small tributaries and that flows long distance;

12. ''**Protection**'' means enabling satisfaction of the need of the present generation by taking into account interest of the next generation by keeping the ecology of the environment and developing natural resources;

13. ''**Person**'' means natural person or juridical person.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be applicable on rivers and river sides and climate region within Addis Ababa City Government.

**4. <u>Gender Reference</u>**

Provision of this Regulation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## ክፍል ሁለት
## መቋቋም፣ ተጠሪነት ፣አደረጃጀት ስልጣንና ተግባር

### ፭. መቋቋምና ተጠሪነት

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ከዚህ በኋላ "ፕሮጀክት ጽህፈት" ቤት እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የቴክኒክ ስራውን በተመለከተ ግን ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

### ፮. አደረጃጀት

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ፡-

፩. የስራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ፤

፪. ዳይሬክተር፤

፫. ምክትል ዳይሬክተር፤

፬. ዋና የቴክኒክ አማካሪ፤ እና

፭. ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

### ፯. ዋና መስሪያ ቤት

፩. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት በከተማዉ ማእከል ደረጃ ይሆናል፤

፪. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## PART TWO
## ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY, ORGANIZATION, POWER AND FUNCTION

### 5. Establishment and Accountability

1. The Addis Ababa City Government Rivers and River sides Development and Climate Change Adaptation Project Office, hereinafter referred to as "project office", is hereby established having distinct personality;
2. The Project Office shall be accountable to the board; however, regarding technical activities, it shall be accountable to the the city manager.

### 6. Organization of the Project Office

The project office shall have :

1. A board of management hereinafter referred as **"the board"**;
2. General Manager;
3. Deputy Manager;
4. Chief Technical Advisor; and
5. Other necessary departments and employee.

### 7. Head Office

1. The head office of the project office shall be at the City center level;
2. The project office may have branches as may be necessary.

**፰. <u>የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>**

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የከተማዋን ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች መነሻ ሁኔታዎች በሚመለከት መረጃን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፤

፪. ወንዝ ዳርቻ ላይ ስለሚኖረው ህብረተሰብ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥናቶችን ያካሂዳል፤

፫. የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ወሰን ይለያል፤

፬. በጥናቶች ውጤትና በማስተር ፕላኑ መሠረት ከወንዝ ዳርቻዎች ለሚነሱ የህብረተሰብ ክፍሎች በህጉና በስሌቱ መሠረት ተገቢው ካሳ እንዲከፈላቸው ያደርጋል፤

፭. የወንዝ ዳርቻዎችን በማስተር ፕላኑና በሚደረጉ ዝርዝር ጥናቶች መሠረት ይዞታውን ያስከብራል፤

፮. ስለ ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች አያያዝና አጠቃቀም ለአካባቢው ህብረተሰብ በተለያዩ ዘዴዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ያከናውናል፤

፯. በአደገኛና በማንኛውም ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከተበከሉ ወንዞች ውስጥ ቆሻሻዎቹን ያወጣል፣ የወንዝ ዳርቻዎችንም ያፀዳል፤

፰. ማንኛውንም ወደ ወንዝ የሚለቀቅ ወይም የሚጣል ቆሻሻዎችን ወንዙን እንዳይበክሉ ስልት ነድፎ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፤

፱. የወንዝ ዳርቻዎች ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ዲዛይናቸው ተጠንቶ እንዲተገበር ያደርጋል፤

፲. ለጎርፍ አደጋ የተጋለጡ የወንዝ ዳርቻዎችን በመለየት የመከላከል ስልት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

**8. <u>Power and Function of the Project Office</u>**

The project office shall have the following powers and functions:

1. Collect and organize data and baseline information of Addis Ababa city rivers and river sides;
2. Conduct socio-economic study of the community living in river sides;
3. Delineate boundary of rivers and river sides;
4. Based on study result and master plan of the city, cause compensation be paid as per the law and valuation for the society vacated from the river sides;
5. Demarcate and legalize river banks as per the master plan and detail studies to be conducted;
6. Perform activities of awareness creation to the local community on how to use and handle rivers and river sides using various methods;
7. Remove hazardous and any solid and liquid wastes from polluted rivers and clean river sides as well;
8. Introduce and follow up the implementation of a system of preventing pollution of the rivers from any solid and liquid wastes thrown or drained in there respectively;
9. Cause implementation of design of river banks in standardized manner;
10. Identify areas which are vulnerable to flood, and design and implement prevention strategy;

፲፩. በዲዛይኑ መሠረት ወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች በአግባቡ ለምተውና ፀድተው ለከተማው ህብረተሰብ የመዝናኛና የመናፈሻ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፣ ሲጠናቀቁ ለሚመለከታቸው አካላት ያስረክባል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፣

፲፪. በጥናት ላይ ተመስርቶ ለከተማ ግብርናና ሌሎች አገልግሎቶች የሚውል ቦታ ይለያል፣ ለተገቢው አገልግሎት መዋሉን ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

፲፫. ፕሮጀክት በመለየት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር ድርጅት ወይም ኩባኒያ እንዲያለማ በማድረግ ለዕውቀት፣ ለክህሎትና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፲፬. በከተማዋ የሚገኙ የማምረቻ እና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በአካባቢው ላይ የሚያደርሱትን አሉታዊ ተፅዕኖ አጠቃላይ ሁኔታ የሚያስረዳ የመረጃ ቋት ያደራጃል፣

፲፭. በከተማ እየተከሰተ ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ያጠናል፣ ቋሚ መረጃ የሚሰበሰብበትን ስልት ይነድፋል፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

፲፮. ከአየር ንብረት ለውጥ መከላከልና ማጣጣም ጋር የተያያዙ ፕሮጀክቶችን ይነድፋል፣ ድጋፍ ከሃገር ውስጥና ውጭ ያፈላልጋል፣ ድጋፍ ሲገኝ የሃገሪቱን የፋይናንስ ህግ በሚፈቅደው መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፲፯. ከተማዋ ከሌሎች ከተሞች ጋር በዘርፉ የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራት ያደርጋል፣ ተሞክሮዎችን ይወስዳል፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ይቀምራል እንዲሁም ይተገብራል፡፡

11. Cause rivers and river banks serve as recreational center for residents of the City by cleaning up and developing properly based on the design; transfer to the concerned bodies upon completion; details shall be determined by directive;
12. Identify areas to be used for urban agriculture and other services based on study; follow up that it is used for the purpose sought and provide appropriate support;
13. Facilitate conditions for the transfer of knowledge, skill and technology by identifying a project and letting domestic or foreign organization or company to develop it;
14. Develop data base system showing the extent of adverse effect the manufacturing industries and service providing institutes within the City have on the environment;
15. Conduct study on the climate change of the City and design a system to collect information permanently and follow up the way by which such will be implemented;
16. Design projects on climate change mitigation and adaptation mechanisms; search for domestic and foreign funds and where found, it used as per the country’s financial law;
17. Cause the City to have strong correlation with other sisterly cities; adopt, compile and implement best practices thereof.

## ፱. ስለ ሥራ አመራር ቦርድ

፩. የቦርዱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ይሆናል፤

፪. የስራ አመራር ቦርዱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ከ፱ እስከ ፲፩ አባላት ይኖሩታል፤

፫. አባላቱ ለፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ሥራ ቅርበት ካላቸው ተቋማት በከተማዉ ሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በከንቲባው ይሰየማሉ፡፡

## ፲. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

፩. አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች እንደ ተጠበቁ ሆነው ቦርዱ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፤

፪. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ መወጣቱን ያረጋግጣል፤ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚመሰረቱ ግንኙነቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤

፫. በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዳይሬክተር የሚቀርብ ለትን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የበጀት አጠቃቀም ሪፓርት ያጸድቃል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዉጪ ኦዲተር ይሰይማል፤ የኦዲት ሪፖርቱን መርምሮ ያጸድቃል፤

፬. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የበታች ኃላፊዎች እንዲመድቡና እንደአስፈላጊነቱ እንዲሰናበቱ ያደርጋል፤

፭. በፕሮጀክት ፅህፈት ቤቱ የሚቀርብለትን የፕሮጀክት ሰራተኞች የስራ መመሪያ ላይ ግብአት ይሰጣል፤ ክፍያዎችንም ይወስናል፤ የተመደበ ለት በጀትና ከዕርዳታ የሚያገኘው ገንዘብ በአግባቡ ለታለመለት ተግባር እንዲዉል ይደግፋል፤ ይከታተላል፤ በአፈፃፀም ችግሮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 9. Management Board

1. The board shall be accountable to the Mayor of Addis Ababa City;
2. The board shall have 9-11 members extracted from the concerned public institutions;
3. Members of the Board shall be appointed by the Mayor upon recommendation of the City Manager from institutions relevant to the activities of the Project Office.

## 10. Power and Function of the Board

1. Without prejudice to the relevant legal provisions, the Board shall be superior decision making body on the affairs of the Project Office;
2. Ensure the proper implementation of the powers and functions by the Project Office; examine and endorse relationships with third parties;
3. Approve annual performance and budget utilization reports of the project office tabled by the Director; assign external auditor where it finds necessary; evaluate and approve the report thereof;
4. Cause lower officials of the Project Office assigned and dismissed as may be necessary;
5. Give feedback on working manual of the project submitted by the Project Office; decide on payments; support and follow up that the budget and aid utilized for the function sought.

## ፲፩. የቦርዱ ስብሰባ

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከአባላቱ አንድ ሶስተኛው ከጠየቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
3. የቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
4. ማንኛወም የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈዉ በስብ ሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በአብላጫ ድምፅ ሆኖ ድምፁ እኩል ከሆነ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ወገን ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፤
5. ቦርዱ የራሱን የዉስጥ አሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤
6. ቦርዱ የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን ዳይሬክተር በቦርድ ስብሰባ ላይ በድምፅ እንዲሳተፍና ፀሀፊ ሆኖ እንዲሰራ ሊሰይም ይችላል፡፡

## ፲፪. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት

1. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፤ ሰራተኞችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፤
2. ለፕሮጀክት ፅህፈት ቤቱ የሚያስፈልገውን አመታዊ የስራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ በሚመ ለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፤ ሲጸድ ቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. ወቅታዊና አመታዊ ሪፖርት ለቦርዱ እና ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
4. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፤

## 11. Meeting of the Board

1. The Board shall hold its regular meeting once in a month;
2. Without prejudice to the provision of sub-article 1 of this Article, extra ordinary meeting may be called where the chairperson or one-third of the members so request;
3. There shall be a quorum where more than half of the members are present;
4. Any decision of the Board shall be passed by majority vote of the members present in the meeting and in case of a tie the chairperson shall have a casting vote;
5. The Board may issue directives of its own internal working procedure;
6. The Board may nominate Director of the Project Office to participate with vote and as a secretary in the meeting of the Board.

## 12. Power and Function of Director of the Project Office

1. Superiorly direct the Project Office; employ or dismiss employee in accordance with appropriate law;
2. Prepare and cause the necessary budget and annual plan of the Project Office approved by the concerned body; implement same upon approval;
3. submit periodical and annual report to the Board and concerned body;
4. Enter into relationship with third parties representing the Project Office;

፭. ለሥራዉ ዉጤታማነት አስፈላጊ በሆነ መጠን ለምክትል ዳይሬክተሩ ዉክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፮. የፕሮጀክት ፅህፈት ቤቱ የውስጥ መመሪያዎች እንዲዘጋጁ በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ ግብአት እንዲሰጥበት ለቦርዱ ያቀርባል፤ በሥራ አስኪያጁ ሲጸድቅ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፡፡

**፲፫. <u>የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ምክትል ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት</u>**

፩. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ምክትል ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዋናው ዳይሬክተር ይሆናል፤

፪. ምክትል ዳይሬክተሩ በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዕቅዶች ዝግጅትና አፈጻጸም ዋና ዳይሬክተሩን በማገዝ ይሠራል፤

፫. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን ስራ በምክትል ዳይሬክተርነት ይመራል፤

፬. ዳይሬክተሩ በማይኖሮርበት ወይም መሥራት በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

፭. ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

**፲፬. <u>የቴክኒክ ዋና አማካሪ ኃላፊነትና ተግባር</u>**

፩. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን የስትራቴጂክ ዓላማዎች ለማስፈፀም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነዶችንና የትብብር ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ያቀርባል፤

፪. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን አደረጃጀትና በስራ አፈፃፀም ስልት ረገድ ሊያደርግ የሚገባውን ለውጥ በየጊዜው እየተከታተለ ሃሳብ ያቀርባል፤

5. Delegate the Deputy Director to the extent necessary to make the activity effective;
6. Cause the preparation of and submit internal directives of Project Office, as may be necessary, for feedback of the Board; follow up the implementation thereof upon approval by the Manager.

**13. <u>Power and Duty of the Deputy Director of the Project Office</u>**

1. The deputy director shall be accountable to the Director of the Project Office;
2. The deputy Director shall work supporting the Director in the preparation and implementation of plans of the Project Office;
3. Direct the activities of the Project Office in the position of Deputy Director;
4. Represent the Director in his absence or in the case of his incapacity;
5. Perform such other activities designated by the Director.

**14. <u>Power and Function of the Chief Technical Advisor</u>**

1. Design and prepare memorandum of understanding and cooperation programs regarding activities carried out with other organizations with the view to execute strategic objectives of the Project Office;
2. Timely follow up and submit recommendation regarding any change on the organizational structure and ways of performing activities of the Project Office;

፫. ዳይሬክተሩ በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ውስጥና ውጪ በወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ጉዳዮች የሚያደርጋቸውን ስብሰባዎች ውሳኔና ስምምነት አፈፃፀም ይከታተላል፤

፬. በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ላይ ይሳተፋል፤

፭. ለፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የተቀጠሩ ወይም የሚሠሩ የውጭ አማካሪዎች የሥራ ክንውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡

## ክፍል ሦስት
## በጀት፣የሂሳብ መዛግብት፣ ንብረት እና የሰው ኃይል አስተዳደር

### ፲፭. በጀትና የሂሳብ መዛግብት

፩. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በጀት በአስተዳደሩ ይመደባል፤

፪. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የተሟሉና የተረጋገጡ የሂሳብ መዛግብት በከተማዉ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሠረት ይይዛል፤

፫. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ እና እንደአስፈላጊነቱ በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ይመረመራል፡፡

### ፲፮. ስለ ንብረት አስተዳደር

፩. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የራሱ ንብረቶች ይኖሩታል፤

፪. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ንብረቶቹን በኃላፊነት ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤

3. Follow up decisions and agreements made on meetings by the Director on affairs of rivers and riverbanks within or outside the Project Office;
4. Participate in the preparation of strategic plan of the Project Office;
5. Monitor and evaluate the works of foreign consultants employed or working for the Project Office.

## PART THREE
## BUDGET, BOOK OF ACCOUNTS, PROPERTY AND HUMAN RESOURCE ADMINISTRATION

### 15. Budget and Book of Accounts

1. Budget of the Project Office shall be allocated by the City Government;
2. The project office shall keep complete and authenticated book of accounts in accordance with the finance administration law of the City Government;
3. Book of accounts and financial documents of the Project Office shall be examined by office of the Auditor General at the end of the fiscal year and as may be necessary.

### 16. Property Administration

1. The project office shall have its own properties;
2. The Project Office shall administer and control properties thereof;

፫. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የስራ ዘመኑ ሲጠናቀቅ ንብረቶቹን በፋይናንስ ህግ መሠረት ለሚመለከተው አካል ያስረክባል፡፡

3. The Project Office shall handover properties to the concerned body as per the financial law at the expiry of its tenure.

## ፲፯. የሰው ኃይል

፩. ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በተጠናው ጥናት መሰረት የሰው ኃይል መዋቅሩ ሲፈቀድለት ሰራተኞችን ለተወሰነ እና ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥራል፡፡

፪. እንደአስፈላጊነቱ ለሥራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ተጨማሪ ሰራተኞችን ከከተማዉ አስተዳደር እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊጠቀም ይችላል፤ ዝርዝሩን በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 17. Human Resource

1. The Project Office shall recruit employees for definite and indefinite period of time in accordance with the study and permitted human resource structure.
2. The Project Office may use other additional employees from institutions of the City Government and higher education institutions to carry out its tasks as may be necessary. Details shall be determined by directive.

# ክፍል አራት
# ልዩ ልዩ ድንገጌዎች

## ፲፰. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የስራ ዘመን

የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የስራ ዘመን አምስት አመታት ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ሊራዘም ይችላል፡፡

## ፲፱. ስለ መተባበር

ለዚህ ደንብ አፈፃፃም ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፳. ደንቡን ስለማሻሻል

ይህንን ደንብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

# PART FOUR
# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 18. Tenure of the Project Office

Tenure of the Project Office shall be for a period of five years and however, Cabinet of Addis Ababa City may extend it, as may be necessary.

## 19. Duty to Cooperate

Any person shall have an obligation to cooperate for the implementation of this Regulation.

## 20. Amendment

The Addis Ababa City Government Cabinet may amend this Regulation, as may be necessary.

**፳፩. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎችና አሰራሮች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ደንቡ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፪. <u>ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፱ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አባባ**

**ታህሳስ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**21. <u>Inapplicable Laws and Practices</u>**

Any regulation, directive or traditional practice which is inconsistent with this Regulation shall have no effect with respect to matters provided for in this Regulation.

**22. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter in to force as of 19th day of December, 2015.

**Done at Addis Ababa**

**On this 18th day of December, 2015**

**Diriba Kuma**

**Mayor of Addis Ababa City**